22110015

International Baccalaureate®
Baccalauréat International
Bachillerato Internacional

**AMHARIC A1 – STANDARD LEVEL – PAPER 1**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU MOYEN – ÉPREUVE 1**
**AMHÁRICO A1 – NIVEL MEDIO – PRUEBA 1**

Wednesday 11 May 2011 (morning)
Mercredi 11 mai 2011 (matin)
Miércoles 11 de mayo de 2011 (mañana)

1 hour 30 minutes / 1 heure 30 minutes / 1 hora 30 minutos

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a commentary on one passage only. It is not compulsory for you to respond directly to the guiding questions provided. However, you may use them if you wish.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N’ouvrez pas cette épreuve avant d’y être autorisé(e).
- Rédigez un commentaire sur un seul des passages. Le commentaire ne doit pas nécessairement répondre aux questions d’orientation fournies. Vous pouvez toutefois les utiliser si vous le désirez.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un comentario sobre un solo fragmento. No es obligatorio responder directamente a las preguntas que se ofrecen a modo de guía. Sin embargo, puede usarlas si lo desea.





© International Baccalaureate Organization 2011

https://xtremepape.rs/

*ከሚከተሉት ምንባቦች አንዱን መርጠህ አስተያየት ስጥ(ስጪ)፡፡*

**1.**

ያ ለስላሳ የሆነው ጫማው ደግሞ ሃገሩ የተሠራ አንድ ምስማር እንኳ የሌለው ቀርበቱ በቆርበት የተሰፋ ነበር፡፡

አባቴ ወደ ሰማይ ለመግባት የሚፈልግ መንፈሳዊ ሰው ስለ ነበር ጉቦ በቤታችን በር አልገባም፡፡ እንዲሁ ቅን ፈራጅ ነበር፡፡ ከአባቴ የማስታውሰው በደል፣ ይህ የሚከተለው ነው፡፡ ስሙን ባልሳሳት ተፈራ የተባለው ከዋናው ሲታይ የመሬት ድምበረኛ ስለሆነ በመሬት ምክናያት ከአባቴ ጋራ የከራከሩ ነበርና በትንሽ ምክናያት አያሌ ቀን በማሠር አባቴ ቂሙን ተወጣበት፣ ግን ከሚበላውና ከሚጠጣው የእርሱን ድርሻ ያህል ይልኩለት ነበር፡፡

በዚህ ባለሁበት ዘመንና አባቴን በሕፃንነቴ ባወቅሁበት ዘመን መሃከል ያለው ዘመኑ የሚያሳየው መለዋወጥ በኖን ዘመንና በእኛ ዘመን መሃከል የሆነውን የዘመን ርቀት ያህል ለማሳየት ይመስላል፡፡ በእውነት፣ በዚህ ዘመን የነበሩ አባቶቻችን የአፍሪካ መላእክቶች ነበሩ፡፡ ለእሥረኛ እንኳ የቅዱሳን ዓይነት ይሉኝታ /ሞራል/ ነበራቸው፡፡ ሁሉም እንደ ርግብ የዋሃን ነበሩና እንደርግብ ደግሞ ብልሆች ነበሩ እንጂ ብልሃታቸው በልቡ እንደሚሳብ እባብ አልነበረም፡፡ የዘመናቸውን በጎነት ከዚያ ዘመናችን ጋር ስመለከተው እነርሱ መልካሙን ቀን ኑረውት በመልካም ወደ ሌላው ዓለም ዘመቱ፡፡

ተማሪ ቤቱ በስፋት ከእኛ ቤት የተሻለ ነው እንጂ በጥዳት እጅግ የተሻለ አይደለም፡፡ ልክ እንደ እኛ ቤቶች ሁለት ቤት ናቸውና በአንዱ አስተማሪው በሌላው ቤት ደግሞ ተማሪዎች ይኖሩበታል፡፡ አስተማሪው ስለ ቅድስና ድንግል ለመሆን መርጥዋልና ያላገባ ነበር፡፡ መጸለይ ልማድ ሆኖበት በትምሕርት ጊዜ ሲያስተምረን ሳያስበው በመጸለይ ከንፈሩ ሲንቀሳቀስ እናየው ነበር፡፡ ድንገት ግን አእምሮው ሲመለስና የት መሆኑን ሲያውቅ ያፍራልና የሚንቀሳቀሰው ከንፈሩ ዝም ይል ነበር፡፡ የሞተውን ሰው ወደ መቃብር በሰላም ለማሰናበት ፍታት ለመፍታትና የመቃብሩን አፈር ለመባረክ ካልሆነ በቀር ከተማሪ ቤቱ አጥር የሚወጣበት ሌላ ሥራ ለጣቱ የለውም፡፡ ለደብረ ማርቆስ ያላት የመጀመሪያውና የመጨረሻ ዋና ሰዋ እርሱ ነበር፡፡ እንደ መዓረግ ስሙ ርእሰ ደብር ፀጋ ይባላል፡፡ የደስታ ሕይወት አልነበረውም እንጂ በሰው ሁሉ ዘንድ የተወደደ የዋህ ሁሉ ጊዜ የደስታ ፊት ያለው ሰው ነበር፡፡

ከቀን ውስጥ አሥር ሰዓት በመጽሐፍ እንማራለንና በቀን ወይም በዓመት በመሃከሉ አቋርጦ ማረፍ የለውም፤ ደግሞ ያለ መጽሐፍ፣ ሶስት ሰዓት ከማታው ሁለት ሰዓት ደግሞ ገና ሳይጠባ በቃል እንማራለን፡፡ ከሃያ አራት ሰዓት ውስጥ ያለን ትርፍ ጊዜ ዘጠኝ ሰዓት ብቻ ነበርና እንደ ሕፃን ለመጫወት ቀርቶ እንደ ሕፃን እንቅልፋችንን ለመጨረስ የበቃ ጊዜ አናገኝም ነበር፡፡ ስለዚህም እየተማርን ብዙ ጊዜ እንተኛ ነበር፡፡ ከወንበሩ ሊወድቅ አስኪቀርብ ድረስ አስተማሪው እንኳ እያስተማረን ቢተኛ እንጠቃቀስበት ነበርን፡፡ አስተማሪው ሲያጨበጭብ የሚጠራን ደውል ማጨብጨቡ ነው እንጂ በተማሪ ቤት ደውል አልነበረም፡፡ አስተማሪው ሲያጨበጭብ እየተነጫጫን ቀን አንሰማውም ነበር፡፡ በሌሊት ደግሞ ዕንቅልፍ ሲያሸንፈን ፈጥነን አንነቃምና ሁል ጊዜ ወፈር ባለ ዱላ ይሰበስበን ነበር፡፡ አስተማሪያችን ዕንቅልፋችንን እስክንጨርስ ድረስ አይተወንምና ለሌት ለትምሕርት ሲቀሰቅሰን በዱላ አያሌ ጊዜ ይመታን የነበረው እጅግ መራራ ሁኖ ዛሬ ድረስ ይሰማኛል፡፡ ከተማሪ ቤታችንና ከቤት ክርሲቲያኒቱ መሃከል የተሰቀለውን ደውል ቢደውልልን ያለዱላው ከመኝታችን በተነሣን ነበር፡፡ ግን ያ ደውል ከዚህ ለሚበልጥ ሥራ ተሰቅሏልና ለዚህ ለትንሽ ሥራ ልንሠራበት ሕግ አልፈቀደልንም፡፡

ተመስገን ገብሬ፣ *ህይወት*፣ አልፋ አሳታሚዎች (2008)

- የጸሀፊው የትውልድ ስፍራ በምን ቴክኒክ ቀረበ?
- በጽሁፉ ቀደም ያለው መቼት እንደምን ቀረበ?
- ጸሃፊው ሊያስተላልፍ የፈለገው መልእክት ምንድነው?



https://xtremepape.rs/

**2.**

ምንድንነው ቁንጅና እስቲ መለኪያ አምጡ
እንስፈር እንለካው እንወቀው በቅጡ
እንለየው በቅጡ ልኩን እንወቅና
ምንድን ነው ቁንጅና?
በሏ ንገሩና!

ልስልስ ፀጉር ነው ወራጅ እንደሰርዶ
የሚዘፈንለት ፀጉሯ ወርዶ ወርዶ
ቀጥ ያለ አፍንጫ ነው ሰበዝ ነው ስንደዶ
ሆጭ ያለ ጥርስ ነው ነጭ አንደበረዶ
የብረት አሎሎ አይኗ ጉልላቷ
ችምችም ያለ ሣር ነው ቅንድብ ሽፋሽፍቷ
ኮለል ያለ ነወይ ብርሌው አንገቷ
ከሩቁ  የሚታይ ነው ሣንቃ ነው ደረቷ
ጉች ጉች ያለ ነው ብርቱካን ነው ጡቷ

ቋጥረው የሚፈቱት አለንጋ ነው ጣቷ
የላመ ከንፈር ነው ስትስቅ እየሸሸ
ልብን ያራራጠ መንፈስን ያስጓሸ
ጭብጥ የማይሞላ ወገቧ ነው ችቦ
ዙሪያውን በዞራት መቀነት ተውቦ

ስጉብ ነወይ ሆዷ የኖረ ተርቦ
ኩሩ ነው ዳሌዋ እንደሞሉት ገንቦ
ሰልካካ ነው ባቷ እንደየቀንድ ዋንጫ
የውበትን ምሥጢር መጎንጫ መጠጫ
ልቅምነት ነወይ ተረከዘ ሎሚ
ለወይዘሮ አካሄድ ለጫማ ተስማሚ
ምንድን ነው ቁንጅና?
በሏ ንገሩና!

ቁንጅና፣ ቁንጅና
ረቂቅ አካል ነሽ የውስጥ የልቦ
ሥጋ ስላይደለሽ መቼ ትታይና

እንደሚሚሸሸው፣ ሚቆረፍደው
እንደሚሻግተው፣ እንደሚሸብተው
መች ሥጋ ነሽና በስባሹ ፈራሹ
ቁንጅና የት አለሽ ብለው ሰዎች ቢሹ
ብልጠት የሌለበት ፈፁም ትህትና
እሷ ነች ቁንጅና።

ተንኮል የሌለበት ፀዓደ ህሊና
እሷ ነች ቁንጅና።
ለፅውነት ለሀቅ ሌት ቀን ደፋ ቀና
እሷ ነች ቁንጅና።
ካለህ ማካፈሉ ቆረስ ታደርግና
እሱነው ቁንጅና
በተኛበት ሰዓት ሰው ታሞ በጠና
እግዚአብሔር ይማርህ እሱ ነው ቁንጅና።

ባዘነበት ሰዓት ዘመድ ሞተውና
አላህ ይሶብርህ እሱ ነው ቁንጅና።

ቁንጅና ቁንጅና
ረቂቅ አካል ነሽ የውስጥ የልቦና
ሥጋ ስላይደለሽ መቼ ትተይና።

አወል እንድሪስ፣ “ቁንጅና”፣ *የዘመን ቀለማት የግጥም መድብል*፣ ግራፊክ አሳታሚዎች (2006)

– ገጣሚው ውበትን ለማቅረብ የተጠቀመባቸው ቴክነኮች የትኞቹ ናቸው?

– ገጣሚው የተጠቀመበት የድምጽ አቀማመጥና ስርአት የግጥሙን ይዘት ለመረዳት ያለውን ጥቅም አስረዳ።

– ገጣሚው የአንባቢው አመለካከት ላይ ተጽእኖ ለማሳደር የተጠቀመባቸው ቴክኒኮችና ስለግጥሙ ያለህ አጠቃላይ አስተያየት ላይ ሀሳብ ስጥ።



https://xtremepape.rs/